የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኢንፎሜሽንና ኮ/ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ከመጋቢት 9- 14፤ 2018 ዓ.ም
MARCH 18 -23/ 2026

1. በነዳጅ አቅርቦት ዙሪያ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ ቀጥሏል

ኢዜአ፡ መጋቢት 12/2018

በነዳጅ አቅርቦት ዙሪያ በሚፈጸሙ ወንጀሎች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠሉን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ።

በነዳጅ ስርጭትና ግብይት ሂደት ላይ የሚታዩ ሕገ-ወጥ ተግባራትን ለመቆጣጠር በስድስት ክልሎችና በሁለት የከተማ አስተዳደሮች የተጀመረው የተቀናጀ ዘመቻ መጠነ ሰፊ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ሚኒስትሩ ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) ገልጸዋል።

ባለፉት ቀናት በተደረገው ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥርም የተለያዩ እርምጃዎች መወሰዳቸውን ኢዜአ ከሚኒስቴሩ ያገኘው መረጃ ያመለክታል።

በዚህ መሰረትም በሕገ-ወጥ መልኩ ሲዘዋወር የነበረ 250 ሺህ 221 ሊትር ቤንዚን እና 198 ሺህ 432 ሊትር ናፍጣ ተይዞ መወረሱን ሚኒስትሩ ገልጸዋል።

ከተወረሰው ነዳጅ መካከል በሽያጭ ለጥቅም እንዲውል ከተደረገው ውስጥ ከ48 ሚሊዮን 663 ሺህ ብር በላይ ለመንግሥት ገቢ መሆኑን ሚኒስትሩ የገለጹ ሲሆን በአሻጥሩ ተሳትፈው የተገኙ 613 ግለሰቦች በቁጥጥር ስር መዋላቸውን አስረድተዋል።

ከተያዙት ግለሰቦች መካከል የንግድ ጽሕፈት ቤት ኃላፊዎች፣ የቡድን መሪዎች፣ የሬጉላቶሪ ባለሙያዎች፣ የነዳጅ ማደያ ባለቤቶችና ሠራተኞች እንዲሁም በየደረጃው የሚገኙ የጸጥታ አካላት እንደሚገኙበት ጠቁመዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8521963

2. የኢትዮጵያ ባንኮችንና በኢንዱስትሪ ዞኖች የሚያለሙ ባለሃብቶችን ትብብር የሚያጎለብት መመሪያ ተግባራዊ ተደርጓል

ኢዜአ፡ መጋቢት 9/2018

የኢትዮጵያ የግልና የመንግስት ባንኮችንና የኢንዱስትሪ ዞን አልሚ ባለሃብቶችን የወጪ ንግድና ተኪ ምርት አቅም የሚያሳድግ የትብብር መመሪያ ተግባራዊ መደረጉን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለጸ።

ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የኦፐሬሽንና ፓርክ አስተዳደር ዘርፍ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍጹም ከተማ እንዳሉት፤ ባለፉት ዓመታት ከ1 ነጥብ 5 ቢሊየን የአሜሪካን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ የኢንቨስትመንት ፍሰትን የሚያሳልጥ የኢንዱስትሪ ዞኖች ተገንብተዋል።

በአሁኑ ወቅትም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን 11 ልዩ የኢኮኖሚ ዞኖችን፣ ሁለት መካከለኛ ኢንዱስትሪ ፓርኮችንና አንድ የአይ.ሲ.ቲ ፓርክን እያስተዳደረ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የሀገር ውስጥ አልሚ ባለሃብቶችን ለማበረታታት በተከናወኑ ተግባራት አሁን ላይ በኢንዱስትሪ ዞኖች ከተሰማሩ 250 ባለሃብቶች ውስጥ 65 በመቶ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ አልሚዎች መሆናቸውን ተናግረዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_8507815

3. ነዳጅን በቁጠባ በመጠቀም የኢኮኖሚ ጫናውን እንቀንስ፡- ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር ኢቢሲ፡ ረቡዕ መጋቢት 09, 2018

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰተውን የነዳጅ አቅርቦት እጥረት ተከትሎ፣ ዜጎች ያለውን ነዳጅ በኃላፊነት ስሜትና በቁጠባ እንዲጠቀሙ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዓለሙ ስሜ (ዶ/ር) ጥሪ አቀረቡ።

ሚኒስትሩ እንደገለጹት፤ በመካከለኛው ምስራቅ የተፈጠረው ግጭት በዓለም አቀፍ የነዳጅ አቅርቦት ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል በመፍጠሩ፣ የመጣውን የነዳጅ እጥረት ለመቋቋም አላስፈላጊ የትራንስፖርት እንቅስቃሴዎችን በመገደብ ነዳጅን መቆጠብ ይገባል። መንግሥት በዜጎች ላይ የሚደርሰውን የኑሮ ውድነት ጫና ለመቀነስ በነዳጅ ግዢ ላይ ከፍተኛ ድጎማ እያደረገ መሆኑን የጠቀሱት ዶ/ር ዓለሙ፤ ይህም በተለይ በትራንስፖርትና በመሠረታዊ ሸቀጦች ላይ የሚፈጠርን ድንገተኛ የዋጋ ጭማሪ ለመግታት ትልቅ ሚና እንዳለው አስረድተዋል። በዚህም አጫጭር ጉዞዎችን በእግር በመጓዝ፣ ከተናጥል ተሽከርካሪ ይልቅ የብዙኃን ትራንስፖርት አማራጮችን በመጠቀም፣ በቤተሰብ ውስጥ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ቁጥር በመቀነስ በጋራ በመጠቀም እንዲሁም እንደ ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ያሉ አማራጮችን በስፋት እንዲተገበሩ አሳስበዋል። እነዚህን የቁጠባ እርምጃዎች መተግበር በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ለሀገር ማሰብና የኢኮኖሚ ጫናውን ለመቋቋም አቅም የሚሰጥ ተግባር መሆኑንም ሚኒስትሩ አክለው ገልጸዋል።

https://www.ebc.et/Home/NewsDetails?NewsId=4506

4. የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጋር ያለውን አለመግባባት ለመፍታት ከኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት የተሰጠውን የመፍትሔ ሐሳቦች ተቀብሎ ተፈጻሚ እንደሚያደርግ አስታወቀ፡፡

ሪፖርተር፡ መጋቢት 7 ቀን 2018 ዓ.ም

ጀምሮት የነበረውን ክስ በይፋ እንደሚያቋርጥም ገልጿል፡፡ በሁለቱ ንግድ ምክር ቤቶች መካከል ለተፈጠረው አለመግባባት አንድ ምክንያት የነበረው የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ከኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በኪራይ ሲጠቅምባቸው ለነበሩ ቢሮዎች ኪራይ አልከፍልም በማለቱ እንደሆነ ይታወሳል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በቢሮው የመገልገል መብት አለኝ በማለት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ጭምር ወስዶ የምገለገልባቸው ቢሮዎች በኃይል ተወስደውብኛል በማለት የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤትን ከሶ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት መፍትሔ ይሆናሉ ያላቸውን ዝርዝር ጉዳዮች ካሳወቀ በኋላ የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በቀረቡለት የመፍትሔ ውሳኔዎች መስማማቱን በማወሳወቅ አለመግባባቱ ሊረግብ ችሏል፡፡ በዚህም መሠረት የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በኢትዮጵያ ንግድ ምክርቤት ላይ የመሠረተውን ክስ በማንሳት የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ያቀረባቸውን የመፍትሔ ሐሳቦች ተቀብሎ እንደሚፈጸም አስታውቋል፡፡ ከኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ጋር በቀጣይ መልካም ግንኙነት ለማጠናከር እንደሚፈልግ የካቲት 27 ቀን 2018 ዓ.ም. በጻፈው ደብዳቤ ያስታወቀው የአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት በመውሰዱ ምክንያት የኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት ለጠበቃና ለሌሎች ያወጣቸውን ወጪዎች ሁሉ ለመመለስ መስማማቱን ገልጿል፡፡

https://ethiopianreporter.com/153478/

5. Savings, Investment Decline Overshadow Export Boom in UNDP Profile

The Reporter: March 21, 2026

In its latest quarterly economic profile, the UN Development Programme (UNDP) warns that a sharp decline in gross national savings and investment over the past several years could spell trouble ahead despite record growth in export revenue.

Gross national savings have fallen from nearly 30 percent of GDP in 2018 to around 20 percent in 2025, while the investment rate has dropped even more steeply, from 35.3 percent to 20.1 percent over the same period, according to UNDP.

"These trends suggest reduced fiscal space and reduced capital formation, which could constrain future growth," warns the report.

It contrasts the trend with a 53 percent gold-driven surge in Ethiopia's half-year export revenue, raising concerns over sustainability, structural imbalance, and long-term economic resilience.

Export earnings have jumped from USD3.3 billion in the first half of 2025 to USD five billion during the same period in 2026, reflecting both favorable global commodity prices and the effects of ongoing macroeconomic reforms.

However, the UNDP report underscores that much of this expansion is concentrated in a single commodity.

https://www.thereporterethiopia.com/49798/

6. Importers Stand to Gain Partial Goods Release Under Proposed Customs Reform

The Reporter: March 21, 2026

Importers facing cash constraints may soon be allowed to clear goods in installments under a proposed amendment to the Customs Proclamation.

The draft law introduces provisions allowing goods declared under a single entry to be released in parts when importers are unable to pay full duties and taxes upfront. A planned consultation meeting with stakeholders on the draft customs proclamation amendment was postponed after parliament failing to meet quorum, delaying discussions on a reform package that signals one of the most comprehensive overhauls of Ethiopia's customs system in years.

https://www.thereporterethiopia.com/49816/

7. Foreign currency reserves surge over 209% as CBE undergoes major institutional, lending policy overhaul

Capital: March 22, 2026

The Commercial Bank of Ethiopia (CBE) has reaffirmed its position at the forefront of the financial industry, bolstered by new capital and a strong balance sheet following the resolution of state-owned enterprise (SOE) obligations. This revitalization at the micro level is reflected in macroeconomic success: the fiscal year 2024/25 has concluded with a notable improvement in the country's current account balance, highlighting a period of significant economic stabilization.

The recently released third edition of the Financial Stability Report reveals that CBE's systemic importance gained considerable traction during the fiscal year ending June 30, 2025. The report, which offers a thorough assessment of the Ethiopian financial sector's health, credits this growth to the implementation of bold macroeconomic reforms during the period.

According to the report, Ethiopia's only systemically important bank (SIB) increased its market share, reversing a declining trend observed in previous years. CBE successfully passed all three stress tests conducted as of June 2025, which evaluated its resilience to credit, liquidity, and foreign exchange risks. As a result, despite existing market concentrations, the systemic risk posed by this SIB is now deemed low.

The report outlines that CBE is undergoing extensive institutional reforms, including a comprehensive overhaul of its lending policies to government enterprises, workforce capacity building, and the enhancement of its institutional frameworks. Additionally, the bank is strengthening its capital buffers through a government capital injection and concessional financing from the World Bank. "In doing so, the bank will continue to play a major role in sustainably supporting Ethiopia's economic development," the report states.

https://capitalethiopia.com/2026/03/22/foreign-currency-reserves-surge-over-209-as-cbe-undergoes-major-institutional-lending-policy-overhaul/

8. Ethiopia Wins Global Finance Award as Central Bank Drives Bold Market Reforms

ENA: March 17, 2026

The National Bank of Ethiopia (NBE) has accelerated financial sector reform by shifting toward an interest rate-based, inflation-targeting monetary policy and adopting a market-based foreign exchange regime since 2024.

The central bank's efforts have been internationally recognised, with the NBE winning the "*Payments and Market Infrastructure Development – Wholesale Award 2026"* from Central Banking, following a major overhaul of Ethiopia's core financial infrastructure.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_8505125